# ቅዳሴ

## የኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያን እውነተኛ ሰማያዊ ገጽታ

«... አባቴ እኔን እንደሾመኝ እኔ ደግሞ በመንግሥቴ ከማዕዴ ትበሉና ትጠጡ ዘንድ በአስራ ሁለቱም በእስራኤል ነገድ ስትፈርዱ በዙፋኖች ትቀመጡ ዘንድ ለመንግሥት እሾማችኋለሁ።» ሉቃ 22፥ 29 - 30

በዲ/ን በረከት አዝመራው



«አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነስቷአል። ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ በክርስቶስ ደግሞ ህያዋን ይሆናሉና።» 1ኛ ቆሮ. 15፥20-21



«እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል፤ ብርቱ የሆነ በእርሱ ለእኔ ታላቅ ሥራን አድርጓልና።» ሉቃ. 1፥49

# መግቢያ

## በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን፡፡

ቅዳሴ እግዚአብሔር ለሚወዳቸው ወገኖቹ ያዘጋጀው የመንግሥተ ሰማያት ዘላለማዊ ማዕድ ነው፡፡ ቅዳሴ በዚህ ዓለም የሚደረግ ነገር ግን በሰማያዊት መቅደስ የሚፈጸም ምስጢር ነው፡፡ ከዚህ ሰማያዊ ባሕርዩ የተነሳም ተመርምሮ የማያልቅ ዕውቀት፣ ታይቶ የማይጠገብ ሰማያዊ ብርሃን፣ ተወስዶ የማይልቅ ጸጋ ተሸክሟል፡፡

ከዚህ ሰማያዊና ጥልቅ ባሕርዩ የተነሳ ይመስላል፣ አባቶች ብዙ ትንታኔ ሳይጽፉበት ክፍት አድረገው የተውት፡፡ በርግጥም ስለዚህ ሰማያዊ እውነታ ደፍሮ መጻፍ ጥልቁን ምሥጢር በራስ አቅም እንደመወሰን ስለሚሰማ ያስፈራል፡፡ ይህን መጽሐፍ ለመጻፍ ስጀምር ይህ ፍርሃት ደጋግሞ ይሰማኝ ነበር፡፡ በእውነት ከእኔ የተሻሉ ሰዎች ቢጽፉት በጣም ደስ ይለኝ ነበር፡፡ ነገር ግን ከዚህ የባስ ሌላም ፍርሃት ሁሌም ያሳስበኛል ፡፡

በታሪክ ትውፊታቸውን አጥተው ባዶ እጃቸውን የቀሩ፣ መንፈሳዊ የሕይወት ምንጫቸው ደርቆባቸው ምእመናኖቻቸው በመንፈሳዊ ሕይወት ጥም የታመሙባቸው ምዕራባውያን አብያተክርስቲያናት የዚህ ሁሉ ምንጩ ኦርቶዶክሳዊ የቅዳሴ ትውፊትን መልቀቃቸው መሆኑን ተረድተው ወደርሱ ለመመለስ በሚፈልጉበት ሰዓት፣ ይህ እነርሱን ለዚህ ያበቃ ቀውስ ከእኛ ቤት ሰተት ብሎ ሲገባ እያዩ እንዴት ዝም ማለት ይቻላል? ስለዚህ በበቂ ባይሆንም እንኳን ጨኸቱን መጀመር ይገባል ብዬ በማመን ጀመርኩት፡፡

ይህንን መጽሐፍ ለመጻፍ የመጀመሪያው ችግር የማጣቀሻ መጽሐፍ አለመኖር ነበር፡፡ ስለዚህ ከራሱ ከመጽሐፈ ቅዳሴ በተጨማሪ በሌሎች ኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናት የተጻፉ መጻሕፍትን መጥቀስ ግድ ሆኗል፡፡ በግብጻዊው ኦርቶዶክሳዊ አባት አባ ታድሮስ ማላቲይ የተጻፈው «Christ in Eucharist» የተሰኘው መጽሐፍና በታዋቂው ኦርቶዶክሳዊ የሥነ ቤተክርስቲያን ሊቅ አባ አሌክሳንደር ስሼሞማን የተጻፈው «The Eucharist Sacrament of the kingdom» የተሰኘው ድንቅ መጽሐፍ እንደማጣቀሻ የተጠቀምኩባቸው ዋና ዋና መጻሕፍት ናቸው፡፡ ዲክስ ግሪጐሪ የተባለ ሰው ለአስራ አራት ዐመት ያህል ስለጥንታዊ «የቅዳሴ ቅርጽ» ካጠና በኋላ የጻፈው «The shape of the liturgy» የተሰኘው ታሪክ አዘል መጽሐፍም ሌላ ጥሩ ማጣቀሻ ነበር፡፡

እንግዲህ ይህ መጽሐፍ ፍጹም እንከን የሌለው የተዋጣለት እንዳልሆነ ለኔው ለራሴም ይሰማኛል፡፡ ጥልቁን የቤተክርስቲያን ዕውቀት ተሸክመው ቁጭ ያሉ አባቶች ካሉ ቢያነስ ስህተቱን ለማረም ብቅ ይላሉ ብዬ አምናለሁ፤ ከሌሉም እርሱው እግዚአብሔር ስለ ቤተክርስቲያኑ ሲል እውነቱን ይገልጥልናል ብዬ አምናለሁ፡፡

ከአዘጋጁ

## 1. መቅድም

## «የእግዚአብሔር ድንኳን»[1] በሰዎች መካከል

ልዑል እግዚአብሔር በሰዎች መካከል ሊያድር ያልፈለገበት ዘመን የለም። የሰው ልጅም ከእግዚአብሔር ጋር ሆኖ ያልተደሰተበት፣ ከእግዚአብሔር ተለያይቶም ያልተከፋበት ዘመን የለም። ቸሩና ርህሩሁ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ስጦታ ይሆን ዘንድ ስነፍጥረትን ቢፈጥርም ሰው ሰጪውን ከተለየ በስጦታው ሊደሰት እንደማይችል ለማሳየት ከእርሱ ጋር ሊያኖረው የሚያስችለውን ትዕዛዝ ሰጠው። የሰው ልጅም ፈጣሪውን ትቶ በፍጥረት መደሰት እንደማይችል የሰው ዘር ታሪክ በራሱ ምስክር ሆኗል። በተቃራኒው ግን በልዩ ልዩ ዘመናት በሰዎች መካከል ያደረች የእግዚአብሔር ድንኳን ለሰዎች ደስታ ስትሆን በመጽሐፍ ቅዱስ ተመልክተናል።

### ሀ. እግዚአብሔርና ሰው በኤደን ገነት

ስለሰው ልጆች ሲል ፍጥረትን የፈጠረ ሰውን ወዳጁ እግዚአብሔር በደስታ ይኖር ዘንድ ሰውን የእግዚአብሔር ቤት በሆነች በኤደን ገነት አስቀመጠው። አባታችን አዳም በገነት ሲኖር እግዚአብሔርን እያመሰገነ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ካህን ሆኖ ይኖር ነበር። በአዳም ውድቀት የመጀመሪያውን ትምህርት አገኘን። ይህውም፣ የሰው ደስታው የእግዚአብሔር ስጦታ ብቻውን ሳይሆን የእግዚአብሔር በመካከሉ መገኘቱ መሆኑ ነው። ከበደሉ በፊት የደስታ ቦታ የነበረችው ገነት ከእግዚአብሔር በተለየ ጊዜ የሃዘን ቦታ ሆናዋለችና። «ነፍስ እግዚአብሔርን ገነቷ አድርጋ ታስበዋለች፤ ምንም አይነት ዓለማዊ ነገር ባታገኝም በእርሱ ትደሰታለችና! ከእግዚአብሔር ከተለየች ግን በገነት ብትኖር እንኳን ከሲኦል ጋር እኩል ነው»[2]። በዚህም የሰው ደስታው በገነት /እግዚአብሔር ከሌለበት/ ሳይሆን በገነት ከሰው ጋር በነበረው በእግዚአብሔር መሆኑ ታወቀ። ምንም እንኳ ሰው በገነት ከእግዚአብሔር ጋር መኖሩ ባይቀጥልም እግዚአብሔር በሰዎች መካከል ለዘለዓለም ለሚያድርባት ለቤተክርስቲያን ምሳሌ ሆናለች። ገነት የቤተክርስቲያን፣ ዕፀ ሕይወት የጌታችን፣ ፍሬዋ የስጋወደሙ፣ በገነት መካከል የሚፈሱት ወንዞች[3] የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌዎች ናቸውና። በገነት መካከል የነበረው ክፉና ደጉን የሚያሳውቀው የእውቀት ዛፍም በራሱ መልካም የሆነ ነገር ግን በዲያብሎስ ሃሳብ /ትርጓሜ/ ልንቀበለው የማይገባ የዕውቀት ምሳሌ ነው።

---

1. ራዕይ 21 ፥ 3

2. «The soul considers God het paradise, she enjoys Him even if she doesn't attain any worldly matters! To be separted from God, even if she lived in paradise, would be equivalent to being in hell! » God, Fr.Tadros Y malaty

3. ዮሐ. 7፥ 38 -39

## ለ. «የእግዚአብሔር ድንኳን» በጥንት አባቶች መካከል /በዘመነ አበው/

በአዳምና በሔዋን በደል ምክንያት እግዚአብሔርና ሰው ለአያሌ ዘመናት ቢለያዩም በኃጢአት ከባዘነው የሰው ዘር መካከል ከእግዚአብሔር ጋር የተገናኙ አባቶችም ነበሩ፡፡ ነገር ግን በዚህ ዘመን የእግዚአብሔርና የሰዎች ግንኙነት በመሰዊያ ላይ የተመሰረተ ነበር፡፡ አባቶችም እግዚአብሔር በተገለጠላቸው ጊዜ በዚያ ቦታ መሰዊያ ይሰሩ ነበር፡፡[1] ይህም ያለ ምክንያት አይደለም፡፡ በቀደሙት ወላጆቻችን የተገነባው እግዚአብሔርንና ሰውን የለየው የኃጢአት ግድግዳ በክርስቶስ መስዋዕትነት እንደሚፈርስና እግዚአብሔር በሰዎች መካከል ለዘላለም እንደሚያድር የሚያሳይ ትንቢታዊ ድርጊት ነው፡፡ ምንም እንኳን ይህ ምሳሌ ቢሆንም አባቶች በዚህ ተደስተው አማናዊቷን የእግዚአብሔርና የሰዎች የኅብረት ማደሪያ በተስፋ እየጠበቁ ሞቱ፡፡[2]

በዘመነ አበው የነበረው መሰዊያ ሌላም የሚያመለክተው ነገር ነበር፡፡ ሙሴና ኤልያስ በአስራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል ስም የሠሯቸው አስራ ሁለት የድንጋይ መሰዊያዎች በክርስቶስ መሰዋዕትነት የተሰበሰበች፣ በሐዋርያት ላይ የተመሰረተች፣ የክርስቶስ አካል፣ የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ የተባለች የቤተክርስቲያን ምሳሌ ነበሩ፡፡[3]

አባታችን ያዕቆብ በፍኖተ ሎዛ ከእግዚአብሔር ጋር የተገናኘባት ቦታም «የእግዚአብሔር ቤት» ተብላለች፡፡ በዚህችም ቦታ ለአሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች አባት ለያዕቆብ ያልተለመደ አስደናቂ ራዕይ ታይቷል፡፡ የሕዝበ እግዚአብሔር አባት ለሆነው ለያዕቆብ የታየው ራዕይም መሰላል፣ በመሰላሉ የሚወጡና የሚወርዱ መላዕክት፣ ከላዩም እግዚአብሔር ናቸው፡፡ በሐዘንና በድካም ለነበረው ለያዕቆብ «እኔ ከአንተ ጋር ነኝ» የሚለው የእግዚአብሔር ቃል «በእውነት እግዚአብሔር በዚህ ቦታ ነው፤ ይህ ቦታ የእግዚአብሔር ቤት ነው፤ የሰማይ ደጅ ነው»[4] እንዲልና ከሃዘኑና ከድካሙ በኋላ የደስታ ምንጭ ሆኖታል፡፡ ይህም «የሕያው እግዚአብሔር ከተማ፣ በደስታ የተሰበሰቡ አእላፋት መላዕክት ቤት፣ የበኩራት ማኅበር»[5] የተባለች የቅድስት ቤተክርስቲያን ምሳሌ ነበር፡፡

## ሐ. የእግዚአብሔር ድንኳን በዘመነ ኦሪት

በባርነት ሥር ለነበሩት ሕዝበ እስራኤል የመጀመሪያ መልካም ዜና ያድናቸው ዘንድ እግዚአብሔር በመካከላቸው መሆኑ ነበር፡፡ «በግብፅ ያለውን

1.ዘፍ.8፥20፣ 13፥4፣ 22፥9
2.ዕብ.11፥13- 16
3.1ኛ.ነገ.18፥31-32፣ ዘፀ.24 ፥ 4
4.ዘፍ. 28፥15 -17
5.ዕብ.12፥22 - 24

የሕዝቤን መከራ በእውነት አየሁ፤ ከአስገባሪዎቻቸውም የተነሳ ጩኸታቸውን ሰማሁ፣ ሥቃያቸውንም አውቄአለሁ፤ ከግብፅም እጅ አድናቸው ዘንድ ከዚያችም አገር ወተትና ማር ወደምታፈሰው አገር ወደሰፊይቱና ወደ መልካሚቱ አገር ወደ ከነዓናውያንም .. አወጣቸው ዘንድ ወረድሁ»[1] እንዲል፡፡ እግዚአብሔር በመካከላቸው ስለነበረም ጠላታቸውን ድል ነስተው አርነታቸውን አገኙ፡፡ እግዚአብሔር ባለበት ባርነት የለምና፡፡ በበረሃው መካከልም እግዚአብሔር በመካከላቸው መሆኑን ለማሳየት ደብተራ ኦሪትን እንዲሰሩ ታዘዙ፡፡ ይህችም ሰውና እግዚአብሔር የሚገናኙባት «የመገናኛ ድንኳን» ተባለች፡፡ እንግዲህ በበረሃ ለነበሩት ሕዝበ እስራኤል በመካከላቸው የነበረችው የእግዚአብሔር ድንኳን ታላቅ ደስታቸው ነበረች፡፡ ሊወርሷት ቃል ከተገባላቸው ምድር ይልቅ በመካከላቸው ያደረውን እግዚአብሔርን ስለወደዱ «እኔ አብሬአችሁ አልሄድም፤ ሂዱና ከመልአኬ ጋር ሆናችሁ የተስፋይቱን ምድር ውረሱ» ሲላቸው ጌርቃቼውን ቀደው አዝነው ነበር፡፡[2] ያለ እግዚአብሔር ከነዓንን ከመውረስ ከእግዚአብሔር ጋር በምድረ በዳ መኖርን መርጠው ነበረና፡፡

ይህች ድንኳን እስከ ዳዊት ዘመን በመካከላቸው ነበረች፡፡ ቅዱስ ዳዊት ስለዚህች ድንኳን እንዲህ ብሎ ዘምሯል፡፡

«የሠራዊት አምላክ ሆይ ማደሪያዎችህ እንደምን የተወደዱ ናቸው ነፍሴ የእግዚአብሔርን አደባባዮች ትወድዳለች፤ ትናፍቃለች፤ ልቤም ሥጋዬም በሕያው አምላክ ደስ ተሰኘ፡፡ ወፍ ለእርሷ ቤትን አገኘች ዋኖስም ጫጩቶቿን የምታኖርበት ቤት አገኘች፤ የሠራዊት አምላክ ንጉሤም አምላኬም ሆይ እርሱ መሰዊያህ ነው፡፡ በቤትህ የሚኖሩ ሁሉ የተመሰገኑ ናቸው፤ ለዓለምና ለዘላለም ያመሰግኑሃል፡፡... ከአእላፍ ይልቅ በአደባባዮችህ አንዲት ቀን ትሻላለች» መዝ 83/84/፥14፣10፡፡ በዝግባና በግራር በተሰራ ቤተ መንግስት የሚኖረው ታላቁ የእስራኤል ንጉሥ ቅዱስ ዳዊት በፍየል ቆዳ የተሰራችውን ድንኳን እንዴት እንደዚህ ወደዳት ቢባል በዚያ ከእግዚአብሔር ጋር ተገናኝቶ ፍጹሙን ሰማያዊ ደስታ ስለሚያገኝ ነበር፡፡[3]

በሰሎሞን ዘመን የተሰራው ቤተመቅደስም የደብተራ ኦሪትን አገልግሎት ይሰጥ ነበር፡፡ ደብተራ ኦሪትና በኋላም የሰሎሞን ቤተመቅደስ እንዴት መሰራትና ምን ምን ነገሮችን ማካተት እንዳለባቸው እግዚአብሔር በዝርዝር ተናግሯል፡፡

---

1. ዘፀ.3፥ 7- 6

2. ዘፀ. 33፥ 1- 4

3. ዘፀ.35

ይህም እግዚአብሔር ለዘላለም አድሮባት የሚኖር የቤተክርስቲያን ምሳሌ ይሆኑ ዘንድ ነበር።[4]

መ. <u>እውነተኛዋ የእግዚአብሔር ድንኳን፣ ቅድስት ቤተክርስቲያን</u>

ከላይ ያየናቸው ታሪካዊ ክስተቶች እግዚአብጠር በዘመናት ከሰዎች መካከል የተገኘባቸውና ሕዝቡን ደስ ያሰኘባቸው መንገዶች ነበሩ።

ከኤደን ገነት በኋላ የሰውና የእግዚአብሔር ግንኙነት በመስዋዕት ላይ የተመሰረተ ሆኖ ነበር። ይህም እግዚአብሔር በሰዎች መካከል እንዲያድር ሰውና እግዚአብሔር በቅድሚያ በመስዋዕት መታረቅ ስለነበረባቸው ነው። እስከ ክርስቶስ መወለድ ድረስ የቀረቡት መስዋዕቶች ፍጹም ስላልነበሩ እግዚአብሔር በሰዎች መካከል ሲያድርም በፍጽምና አልነበረም።

እግዚአብሔር የወሰነው ጊዜ ሲደርስ ጌታችን ከእመቤታችን በነሳው ሥጋ ተገለጠ። እግዚአብሔር በሰዎች መካከል የተገለጠባት፣ መስዋዕት አድርጐ ሰውና እግዚአብሔርን ያስታረቀባት ሰውነቱን ቤተ መቅደስ ብሎ ጠራት።[1] ይህችም ከብሉይ ኪዳንና ከዚያን በፊት በአለው ዘመን የነበሩ «የእግዚአብሔር ድንኳኖት» ምሳሌ የሆኑላት፣ እግዚአብሔርና ሰው ለዘለዓለም የተገናኙባት በእውነት ቤተ መቅደስ ነች። ቀድሞ በትንቢት «እርሱም ለመቅደስ ይሆናል፣… ብዙዎችም በእርሱ ይሰነካከላሉ..»[2] ተብሎ የነገረለት የጌታችን ሰውነቱም እርሱ ራስ የሆነላት፣ አካሉ የተባለች ቅድስት ቤተክርስቲያን ናት።

ሐዋርያው ስለዚህ ሲናገር «ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆነ አታውቁምን?»[3] ይለናል። በክርስቶስ ስም ተጠምቀን ሥጋውን የበላን ደሙን የጠጣን ክርስቲያኖች ሁሉ ከክርሰቶስ አካል ጋር ተዋሕደን የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ እንሆናለንና። የምእመናን አንድነት ደግሞ የክርስቶስ አካል የቤተክርስቲያን ፍጻሜ ይሆናል። ሐዋርያው የክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም የተካፈሉ ሁሉ በክርስቶስ አንድ አካል መሆናቸውን ሲገልጽ «የምንባርከው የበረከት ጽዋ ከክርስቶስ ደም ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን? የምንቆርሰውስ እንጀራ ከክርስቶስ ሥጋ ጋር ኅብርት ያለው አይደለምን? አንድ እንጀራ ስለሆነ እኛ ብዙዎች ስንሆን አንድ ሥጋ ነን፤ ሁላችን ያን አንዱን እንጀራ እንካፈላለንና» ይላል።[4]

---

4. ዕብ. 8 ፥ 5፣ 8፥ 9 - 12

1.ዮሐ 2፥20

3. 1ኛ.ቆሮ. 6፥19 -20

2. ኢሳ 8፥14 -15

4.1ኛ. ቆሮ. 10፥16 -18

እንግዲህ የክርስቶስ አካል፣ የምእመናን አንድነት የሆነችው ቅድስት ቤተክርስቲያን የትንቢትና የምሳሌ ሁሉ መደምደሚያ፣ የልዑል እግዚአብሔር የዘላለም ማደሪያ መሆኗን እንረዳለን።

ለእስራኤላውያን በአስቸጋሪ የነፃነት ትግልና የበረሃ ጉዞ መከራውን የሚያስረሳና ልባዊ ደስታን የሚያስገኝ ይሆንላቸው ዘንድ በደብተራ ኦሪት በመካከላቸው በረድኤት ያደረው እግዚአብሔር ክርስቲያኖች በዚህ ምድር የሚያገኛቸውን መከራ አልፈው በፍጹም ውስጣዊ ደስታ ይኖሩ ዘንድ በመሰዊያው ላይ በማኅበረ ምእመናን መካከል በረድኤት ሳይሆን በአካል ያድራል። ያኛው ምሳሌ ይህ ግን ፍፃሜ ነውና።

ቅዳሴ በቅድስት ቤተክርስቲያናችን በጣም የተከበረና ከሁሉም በፊት ቅድሚያ የሚሰጠው ሥርዓት ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት ቅዳሴ የቤተክርስቲያን የሕልውና ምንጭም ጭምር ስለሆነ ነው። የክርስቶስ አካል፣ ፍጽምት ፣ ማኅደረ እግዚአብሔር የሆነች ቤተክርስቲያን «የምትገለጠው» በቅዳሴ ጊዜ ክርስቶስ በመሰዊያው ላይ ሲቀመጥ ምእመናን ደግሞ በመሰዊያው ዙሪያ ሲከቡ ነውና። ቅዳሴ የሰማያውያንና የምድራውያን የአንድነት ጉባኤ ነውና በእውነት የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር ላይ የምትገለጥበት ምሥጢር ሊባል ይገባዋል። የግብጽ ቤተክርስተያን «ቅዳሴ የሁሉም ማኅበረ ክርስቲያን /አቅሌሰያ/ ምስጢር ነው። በሁሉም ያለች /ኩላዊት/ እና ድኅንት የሆነች ቤተክርስቲያን በክርስቶስ ቅዱስ አካል ሆና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ወደ አብ የምትቀርብበት ምስጢር ነው። በቅዳሴ ጊዜ ያሉትን ብቻ ሳይሆን በሁሉም ማኅበረ ክርስቲያን /አቅሌስያ/ ስም የሚፈጸም መለኮታዊ ተግባር ነው። ድል የነሱና በትግል ላይ ያሉ አባላት ያሏት ያንዲት ቤተክርስቲያን ምሥጢር ነው»[1] ብላ ታስተምራለች። ከክርስቶስ አካል /ሥጋወደሙ/ የተካፈሉ፣ አረፍተ ዘመን የገታቸው በአጸደ ነፍስ ያሉ ምእመናን ከተዋሐዷቸው የክርስቶስ አካል ጋር የሚገለጡበት፣ ቅዱሳን መላእክት በመሰዊያው ላይ ያለውን መለኮት የተዋሐደውን ነፍስ ግን የተለየውን የክርስቶስን አካል/ሥጋወደሙ/ ለማየት በመሰዊያው ዙሪያ የሚረቡበት[2]

---

1. «The Eucharist is the mystery of the whole ecclesia. It is the coming of the whole redeemed catholic ecclesia to the father in Jasus Christ, as His Holy Body, by the pohcer of the Holy Spirit. This is a devine action done on bhalf of the whole acclesia, not only on behalf of those present at the moment of the celebration but all the members. It is a dvine mystery of one ecclesia, i.e of the triumphant and militant members.» Christ in Eucharist, Fr. Tadros r Malady, PP 171

ይህ የቅዱሳን ኅብረት የቤተክርስቲያን እውነተኛ ትርጉም፣ በምድር ላይ የተሰጠ የመንግስተ ሰማያት ቅምሻ መሆኑ ለቤተክርስቲያናችን ግልጽ ነው። በምድረ በዳ ሲጓዙ ረሃብ እንዳያደክማቸው መና ከሰማይ እያወረደ የመገባቸው፣ ውሃ ጥም እንዳያጠወልጋቸው ውሃ ከአለት እያፈለቀ ያጠጣቸው እግዚአብሔር በስሙ ለተጠራን እስራኤል ዘነፍስ ለተባልን ለክርስቲያኖች ያደረገውን ድንቅ ነገር ተመልከቱ። በዚህ ክፉ አለም ስንኖር ሕይወትን እንዳንራብ ምግበ ሕይወት የሆነ ቅዱስ ሥጋውን፣ ሕይወትን እንዳንጠማ የሕይወት መጠጥ የሆነ ክቡር ደሙን ሰጥቶናልና። ይህንንም ዘወትር የምናገኝበትን ሥርዓት በቅድስት ቤተክርስቲያን መስርቶልናልና።

ጸሎተ ቅዳሴ ፍጽምት የሆነች፣ እግዚአብሔር በመካከሏ ያደረ፣ የክርስቶስ አካል ቅድስት ቤተክርስቲያን «የምትገለጥበት»፣ ሰውን ወዳጁ እግዚአብሔር ራሱን የሕይወት ማዕድ አድርጐ የሚያቀርብበት ምስጢር ነው።

በመሰዊያው ዙሪያ የተሰበሰቡ የምእመናን ኅብረት የቤተክርስቲያን ፍጻሜ ነው ያልነው ያለ ምክንያት አይደለም። በዓለማዊ ስብሰባ ሰዎች ከተሰበሰቡ በኋላ የተመሠረተው ማኅበር የእያንዳንዱ ሰው ድምር ውጤት ብቻ ነው። የቤተክርስቲያን ግን የተለየ ነው። እያንዳንዱ ምእመን ፍጽምና የጐደለው ከኃጢአት ፈጽሞ ንጹሕ ያልሆነ ቢሆንም በምእመናን መሰባሰብ የምትመሰረተው ስለኛ ቅድስና ክርስቶስ የተሰቀለላት፣ የሞተላት የምእመናን ጉባኤ ቅድስት ቤተክርስቲያን ግን ፍጽምት ናት። ይህም የራሷ ሳይሆን በመካከሏ ከሚያድረው ከክርስቶስ ቅድስና የተነሳ ነው። «በውሃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤ እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንበት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ»[1] እንዲል።

እንግዲህ ስለ ቅድስናዋ ሲል ክርስቶስ ያቀረበው መስዋዕት በመካከሏ የሚገኝባት በቅዳሴ ጊዜ የሚሰበሰቡ የምእመናን ኅብረት በእውነት ቅድስት፣ ፍጽምት ትባላለች፤ ናትም።

በሌላ በኩል ምንም እንኳ የሚሰበሰቡት ምእመናን ጥቂት ቢሆኑም በመሰዊያው ላይ የሚገለጠው የክርስቶስ አካል ሙሉው የክርስቶስ አካል እንደሆነ ይህንን አካል የተካፈሉ በአካለ ሥጋ ያሉም የሌሉም ምእመናን ሁሉ በምልዓት አብረው ይኖራሉ። ይህም የቤተክርስቲያን የአንድነቷ ፍጻሜ ነው።

1. ኤፌ.5፥26 - 28

እንግዲህ እያንዳንዱ ቅዳሴ የጥቂት ሰዎች ስብስብ ሳይሆን በሁሉ ቦታ ያለችው የአንዷ ቅድስት ቤተክርስቲያን የማኅበር ፍጻሜ ነው፡፡ ስለዚህም ካህናት በቅዳሴ ጊዜ «ወምስለ ፍጻሜ ማኅበራ ለቅድስት አሐቲ እንተ ላዕለ ኩሉ ቤተክርስቲያን፤ ከሁሉ በላይ ከምትሆን ከአንዲት ቅድስት ቤተክርስቲያን ከማኅበሯም ፍጻሜ ሁሉ ጋር..»[2] እያሉ ይጸልያሉ፡፡

እስካሁን ድረስ የእግዚአብሔር በሰዎች መካከል ማደር የደስታቸው ምንጭ እንደነበረ የተለያዩ ዘመናትን ከፋፍለን አይተናል፡፡ ያለፈው ታሪክ ከምሳሌነት ወደ አማናዊነት ተሸጋግሮ እግዚአብሔር በፍጹም አካሉ ያደረባት ቅድስት ቤተክርስቲያን አማናዊቷና ዘላለማዊቷ የእግዚአብሔር ማደሪያ መሆኗንም ተመልክተናል፡፡ ይህ ምስጢር ዘወትር በቅዳሴ ጊዜ የሚፈጸምልን ምእመናን በእውነት ብፁዓን ነን፡፡ በሥርዓት እንደሚገባ ሆነን የምናስቀድስ በቅዳሴ ጊዜ ከእግዚአብሔር መቀበል ያለብንን ሁሉ የምንቀበል ምእመናን ብፁዓን ነን፡፡ ከህልፈተ ዓለም በኋላ የምትገለጠውን ኢየሩሳሌም ሰማያዊት እንኳን በምድር እያለን እንቀምሳታለንና![3]

ይህም መጽሐፍ ምእመናን በቅዳሴ ሊያገኙ የሚገባቸውን ነገር አግኝተው፣ በመካከላቸው በሚያድረው በክርስቶስ ዘላለማዊ ደስታቸውን ተቀብለው የምስጋና ሕይወት እንዲኖሩ እንዲያግዝ ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡

### 1.2. **የመጽሐፉ ይዘት**

ይህ መጽሐፍ የቅዳሴን ትውፊታዊ ዋጋ ታሪካዊውንና መንፈሳዊ ትርጓሜውን በማጣመር ለምእመናን ስለ ቅዳሴ መጠነኛ ዕውቀት እንዲኖራቸውና ለተጨማሪ መንፈሳዊ ዕውቀት እንዲያዘጋጃቸው ተብሎ የተዘጋጀ ነው፡፡

የመጽሐፉ የመጀመሪያው ክፍል ቅዳሴ በጥንታዊ ቤተክርስቲያን የነበረውን እይታ ያብራራል፡፡ ለጥንታውያን ክርስቲያኖች ቅዳሴ በዋሻ ውስጥ እንኳ ሳይቀር በምሥጢር የሚፈጸሙት፣ የሕይወታቸው ዋና መሠረታዊ ሥራ እንደነበረ ታሪክ ይነግረናል፡፡ ከቅዳሴ ጋር የነበራቸው ጥልቅ ቁርኝትም በጥንታውያን ክርስቲያኖች ዘንድ ለነበረው ጥንካሬ መሠረት እንደነበረ እናያለን፡፡

---

2. መጽሐፈ ቅዳሴ
3. ዕብ.6፥ 4 - 6

በዚህ ክፍልም እነዚህ ክርስቲያኖች ከዚህ ጠንካራ ሕይወታቸው የተረዷቸውን እና በትውፊት ለትውልድ አስረክበዋቸው ያለፏቸውን የቅዳሴ ዋና ዋና እይታዎች በጥቂቱ እናያለን። ይህም ሃሳባቸው ሃሳባችን፣ ሕይወታቸው ሕይወታችን እንዲሆን ይረዳናል።

በሁለተኛው የመጽሐፉ ክፍል ቅዳሴ ለዘመናት ያሳያቸውን «ዕድገቶች» እናያለን። ዕድገት ስንልም መሠረታዊ አላማውንና ይዘቱን ሳይለቅ በተለያዩ የቤተክርስቲያን ታሪካዊ ዘመናት ያለፈበትን መንገድ ማለታችን ነው። ከታሪክ መማር ብልህነት ነውና፤ በዚህ ክፍል የተለያዩ አብያት ክርስቲያናት በታሪክ የገጠማቸውን «የቅዳሴ ቀውስ» እና ምክንያቶቹን እናያለን። በዚህም በዘመናችን በእኛ ውስጥ ሳይታወቀን የገባ ቀውስ ካለ እንመረምረዋለን፤ ከሌለ ደግሞ ቀድመን ለመጠንቀቅ ይበጀናል።

በሦስተኛው የመጽሐፉ ክፍል «የቅዳሴን ቅርጽና» በቅዳሴ ውስጥ ያሉ ጸሎቶችና ሥርዓቶች መንፈሳዊ ትርጉም ለመዳሰስ እንሞክራለን። የቅዳሴ ጸሎቶችና ሥርዓቱ ሰማያዊ ይዘት ያላቸውና የመንግሥተ ሰማያት ብርሃን ያረፈባቸው ስለሆኑ ለመረዳት የልብ ንጽሕናና የመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት ያስፈልጋቸዋል። ከዚህ ከተጻፈው የበለጠ እያንዳንዱ ምእመን እንደ መንፈሳዊነቱ ደረጃ በተሻለ ሁኔታ ሊረዳው ይችላል።የመንግሥተ ሰማያት ምሥጢር ነውና በዘለዓለም ሕይወት እንኳን መርምረን የማንጨርሰው ጥልቅ አምላካዊ ዕውቀት ተሸክሟል። በዚህ ጉዳይ ብዙም የተጻፈ መጽሐፍ ስለሌለ፣ በተቻለ መጠን መንፈሳዊ ትርጉሙን ከዚያው ከቅዳሴው ለመመርመር እንሞክራለን።

በመጨረሻው የመጽሐፉ ክፍል በዘመናችን ለሚታየው ዘርፈ ብዙ የቤተክርስቲያን ችግር ቅዳሴ ሰማያዊ መፍትሔ ሆኖ ቀርቧል። አብዛኞቹ ችግሮች ዋናው ሥራቸው ከዚህ መሠረታዊ ችግር የሚመዘዝ ስለሆነ ቅዳሴን በአግባቡ ተረድቶ በሥርዓቱ መፈጸም ለብዙ ችግሮች መፍትሔ ለመሆን እንደሚችል ይገልፃል። በዘመናችን ጠንካራ ለሚባሉት እህት አብያተ ክርስቲያናት «የቅዳሴ ሕይወት» የጥንካሬአቸው ምንጭ መሆኑን በምሳሌ እናያለን። በጨረሻም በዘመናችን ይህን ጸጋ በምልዐት ለማግኘት ምን ማድረግ እንዳለብን በአጭሩ እናያለን።

# 2.ቅዳሴ በጥንታዊት ቤተክርስቲያን እይታ

## 2.1. የምዕመናን መሰባሰብ፤ የቅዳሴ ቀዳሚ ምሥጢር

«ምእመናን ሳይሰበሰቡ ቅዳሴ የሚጀምር አይኑር»

/ ፍጽሐ ነገሥት፤ በእንተ ቅዳሴ/

ቅዳሴ የአንዲቷ ሰማያዊት ቤተክርስቲያን እውነተኛ ገጽታ እንደሆነ ሁሉ የምእመናን መሰባሰብ ደግሞ የቅዳሴ የመጀመሪያ መሠረት ነው፡፡ «እኔ በመካከላቸው እሆናለሁ» ብሎ ደስ የሚያሰኝ ዘላለማዊ ቃል ኪዳን የገባልን ጌታችን፣ «ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት»[1] በማለት በቅድሚያ ማድረግ የሚገባንን ነገር ነግሮናል፡፡ በዚህ ርዕስ የጌታን ቃል በታላቅ ትጋት በፈጸመች፣ ሰማያዊ ሕይወቷ በትውፊት ደርሶ ለአሁኗ ቤተክርስቲያን መሠረት በሆነው በጥንታዊት ቤተክርስቲያን ለምእመናን መሰባሰብ ይሰጥ የነበረውን ትኩረትና ምስጢራዊ እይታ እንመለከታለን፡፡

### የምእመናን መሰባሰብ በቅዳሴ ጥንታዊ ትውፊት

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሐዋርያት ጋር በቤተ አልዓዛር የአይሁድን ፋሲካ ሲያከብር የቅዳሴ መሠረት ተጣለ፡፡[2] የቤተእስራኤል ጉባኤ መሠረት ይሆኑ ዘንድ አስራ ሁለቱን የያዕቆብ ልጆች የመረጠ እግዚአብሔር እስራኤል ዘነፍስ የተባሉ የምእመናን ጉባኤ የሆነች የቤተክርስቲያን መሠረቶች ይሆኑ ዘንድ ሐዋርያትን ሰብስቦ በመንግስተ ሰማያት ማዕድ ላይ አስቀመጣቸው፡፡[3]

በዚህም በሐዋርያት በኩል የቤተክርስቲያን የአንድነት ምስጢር መሆኑን እንመለከታለን፡፡
በመንፈስ ቅዱስ መምጣት የጌታን ምስጢር ሁሉ የተረዱት ሐዋርያት አባቶቻችችንም ይህን ምስጢር ምእመናንን ሰብስበው በአንድነት የሚፈጽሙ ሆነዋል፡፡[4]

ይህ ሥርዓት በሐዋርያዊት ቤተክርስቲያንም የጸና ሆኗል፡፡ «ለእናንተ ደግሞ አሳልፌ የሰጠሁትን እኔ ከጌታ ተቀብያለሁና» የሚለው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «በመጀመሪያ ወደ ማኅበር ስትሰበሰቡ... »[5] በማለት በእርሱ ዘመን የምእመናን መሰብሰብ ለቅዳሴ ቅድመ ሁኔታ እንደነበረ ይናገራል፡፡ «ለእናንተ ደግሞ አሳልፌ የሰጠ ሁትን እኔ ከጌታ ተቀብያለሁና» በማለቱም ይህ የቤተክርስቲያን ምስጢር ከዚያ በኋላ ሥርዓቱን ጠብቆ በትውፊት የሚተላለፍ ሆኗል፡፡

---

1.ማቴ 18፥ 20
2. ሉቃ. 22፥7 -13
3. ሉቃ.22 ፥29 30
4. የሐ.ሥራ 20፥7
5. 1ቆሮ. 11፥ 18

የሐዋርያት ተከታዮች ሐዋርያውን አበውም ይህን የሐዋርያት ትውፊት ተቀብለው በቀጥታ ለትውልድ አስተላልፈዋል። ይህንንም «ትምህርታችን ከቅዳሴ ጋር የተስማማ ቅዳሴያችንም ትምህርታችን የሚያጸና ነው»[1] ብለው አጽንተውታል።

በዚህ ዘመን ምእመናን ሁሉ በቅዳሴ ተገኝተው ሁሉም ሥጋወደሙ ተቀብለው ይሄዱ ነበር። የታመመ እንኳ ቢኖር ሄደው ያቀብሉት ነበር። ያለህማምና ከባድ ችግር ቅዳሴ የቀረ ሰው ራሱን አውግዞ ከቤተክርስቲያን እንደለየ ይቆጠር ነበር[2]።

ጥንታዊ የቤተክርስቲያን ሕንፃ አሠራርም ለዚህ ምስክር ነበር። አሁን ብዙዎቹ የቤተክርስቲያን ምእመናን እንደሚያስቡት ቅዳሴ የተወሰኑ ሰወች ሥራ ሳይሆን የሁሉም ምእመናን የጋራ ሥራ መሆኑን የጥንታውያን ሕንፃ ቤተክርስቲያኖች አስራር ግልጽ ማሳያ ነው። ለጥንታውያን አብያት ክርስቲያናት ሕንፃ አስራር ዋናው መስፈርት ካህናትና ምእመናን ሥርዓተ ቅዳሴን በንቃት መፈጸም መቻላቸው ነበር።

በቅዳሴ ጊዜ ስላለው የምእመናን ኅብረት /ስብስብ/ የጥንታዊት ቤተክርስቲያን እይታ ከዚህም የመጠቀ ነበር። በጥንታዊት ቤተክርስቲያን የምእመናን ስብስብ ምድራውያንን ብቻ ሳይሆን ሰማያውያንንም ያጠቃለለ መሆኑ በጥንታውያን ሥዕሎች ይታያል። በልባዊ እምነታቸው በጥልቀት ያለውን የእነርሱን እና የሰማያውያንን ኅብረት በሥዕል ያሳዩ ነበር። አንድ የነገረ ቤተክርስቲያን ሊቅ ይህን ሲገልጹ «በብዙ ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት ሥዕላቱ ከማኅበረ ቤተክርስቲያን ጋር የሚሳተፉ፣ የዚህን ምስጢር ትርጉም የሚናገሩ፣ ዘላለማዊ እንቅስቃሴውንና የዜማ ምቱን የሚያሟሉ እንደሚመስሉ ይሰማናል።»[3] ይላሉ።

ይህ መልዕክት አሁንም በቤተክርስቲያናችን ይሰማል። በቤተክርስቲያናችን ጥንታዊ ትውፊት ቅድስትና መቅደሱን የሚለየው ግድግዳ በሥዕላት ይሸፈናል።

ይህ ጥንታዊ ትውፊት አንድ ከባድ መልዕክት አለው፤ ይህ ግድግዳ እግዚአብሔርንና ሰውን፣ ካህናትንና ምእመናንን የሚለይ ሳይሆን በጌታችን ዘላለማዊ የክህነት ሥራ እግዚአብሔርና ሰው ሰማያውያንና ምድራውያን መታረቃቸውን በአንዲት የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን አንድ አካል ሆነው መጠቃለላቸውን የሚያሳይ ነው። ግድግዳውን ሳይሆን በእርሱ ላይ የተሳሉትን በመካከላችን ያሉትን ሰማያውያን ቅዱሳን እንድናይ ይህ የቤተክርስቲያን ትውፊት ይነግርናልና።

---

1. Our teaching is in harmony with the ecucarist and the Eucharist confirms our teaching ST. Iranaeus, Against Heresies 4: 18 ፥5
2. Fr. Alexander Schmemann, Eucharist, pp.24
3. We sense in a number of antient churchs the icons seem to take part in the assembly of the churdh they express its meaning; they provide its external movement and rhythm Alexander schememann. The Euchrist pp.21

ከዚህም በተጨማሪ ሌላ ምሥክር አለን። ጥንታዊ የሆነው ሥርዓተ ቅዳሴአችን የሚናገረው ይህንኑ ነው። ሥርዓተ ቅዳሴን በደንብ የተመለከተ ሁሉ ሌላ ነጋሪ ሳያስፈለገው ይህን ምስጢር ይረዳል። እያንዳንዱ የካህን ጸሎት በምእመናን «አሜን!»፣ እያንዳንዱ የዲያቆን ትዕዛዝ በምእመናን መልስ ይጸናል፤ ይፈጸማል በዚህም ሥርዓተ ቅዳሴ የካህናት ብቻ ሳይሆን የምእመናንና የካህነት የአንድነት ምስጢር መሆኑን እንረዳለን።

በዘመናችን የሚታየው ቅዳሴን ለካህናትና ለተወሰኑ ሰዎች መተው፣ ለቤተክርስቲያን ሥርዓትና የሕይወት ልምድ እንግዳ የሆነ ስርዋጽ ነው። ብዙዎች ሥርዓተ ቅዳሴ በዋነኝነት የክህነት ሥራ እንደሆነ እና እነርሱ ግን ቢኖሩም እንኳን አዳማጭ፣ አዳማቂ እንደሆኑ ያምናሉ። ይህ አስተሳሰብ ቅድስት ቤተክርስቲያንን ከውስጧ ከሚሰሟት ሕመሞች አንዱ ነው። በብዙዎች ዘንድ ለሚታየው በሥርዓተ ቅዳሴ ደስታ ማጣትና መሰላቸት፣ ከዚህም የተነሳ የመንፈሳዊ ሕይወት መድከም፣ አንድ ምክንያት ይህ መሆኑን መረዳት ይገባል።

## ከምእመናን መሰባሰብ ጀርባ ያለ የቤተክርስቲያን ምሥጢር

የምእመናን አንድነት፣ ቅድሰት ቤተክርስቲያን፣ የክርስቶስ አካል ናት። እያንዳንዱ ምእመን ደግሞ የክርስቶስ ብልት ነው።[1] እንግዲህ በምእመናን መሰባሰብ፣ ከምድራዊ አስተዳደራዊ ተቋም የምታልፍ፣ ቅደስት የሆነች የክርስቶስ አካል፣ የቤተክርስቲያን ፍፃሜ ይሆናል።

«የቤተክርስቲያን ፍጻሜ» ማለትም ቅድስት የሆነች፣ የቤተክርስቱያን በሰማያዊ እይታዋ መገለጥ ማለት ነው። የምእመናን ስብስብ እንደማንኛውም ምድራዊ ስብስብ የሺዎች «ድምር» ሳይሆን የክርስቶስ ሰማያዊ አካል መገለጥ ነውና።

ብዙ የቤተክርስቲያንን ጥንታዊ ትውፊቶች የማይቀበሉ አዳዲስ የስነ መለኮት አስተምህሮዎች ብቅ ብቅ ባሉበት በዘመናችን ይህን ጠንቅቀን ማወቅ ይገባናል።

እነዚህ ምድራውያን አስተምህሮዎች ለአምልኮ ስርዓት ብዙም ግድ የሌላቸው፣ ቢኖራቸው እንኳ አንዱን የቅዳሴ ክፍል ከሌላው የሚያበላልጡ፣ አንዱን በጣም አስፈላጊ አንዱን ደግሞ ብዙም የማያስፈለግ እያደረጉ መመደብ የሚቀናቸው ናቸው። ስለቅዳሴ ብንጠይቃቸው ህብስቱና ወይኑ የሚለውጥበትን ጊዜ[2] አጉልተው ሌላውን አሳንሰው የሚናገሩ ናቸው። ይህ አስተምህሮ በቅድሰት ቤተክርስቲያናችን የማይታወቅ እንግዳ ነው።

---

1.1ኛቆሮ.12 27

2. ሕብስቱና ወይኑ የመለወጡን ነገርም ቢሆን በኦርቶዶክሳዊና ሰማያዊ መንገድ ሳይሆን በሳይንሳዊና ምድራዊ መንገድ ለማረጋገጥና ለመተንተን የሚፈልጉ ናቸው።

ይህን ሰማያዊ ምሥጢር የምታውቅ ጥንታዊት ቤተክርስቲያን የአንድ ምእመን ከቅዳሴ መቅረት በጣም ያስጨንቃት ነበር። ከማኅበሯ በማያስገድድ ምክንያት የሚቀሩ ሰዎችን በቆራጥ እርምጃ ታሰናብት ነበር።[1] ይህ ጥንታዊ መረዳት፣ ይህ ጥንታዊ ንቃት በዘመናችን የተረሳ ይመስላል። የዚህን ዝለት፣ የዚህን ቸልተኝነት ውጤትም ማንም ሊነግርን አይገባም፤ እያንዳንዳችን በራሳችን የመንፈሳዊ ሕይወት ቀውስ እናውቀዋለንና!

ለቅዳሴ ስንሰባሰብ ለግል አምልኮ ሊሆን አይገባም። ለቅዳሴ ስንሰባሰብ ከዚህ ዓለም ያልሆነች፣ ነገር ግን ስለ ዓለም መዳን በዚህ ዓለም ውስጥ ያለች ሰማያዊቷ የክርስቶስ አካል ቅድስት ቤተክርስቲያንን «እየገነባን» መሆኑን ልናውቅ ይገባል። ይህን አስመልክቶ አንድ ኦርቶዶክሳዊ ሊቅ «ወደ ቤተክርስቲያን እየሄድኩ ነው ስል ከእነርሱ ጋር ሆኜ ቤተክርስቲያንን «ለመገንባት»፣ በጥምቀት ብልት የሆንኩበትን፣ በቃሉ ምሉዕና ፍጹም ትክክለኛ ትርጉም፣ የክርስቶስን አካል፣ ለመሆን ወደ ምእመናን ጉባኤ እየሄድኩ ነው ለማለት ነው።»[2] ይላሉ።

የቤተክርስቲያን ቅድስና ይህ ነው፤ የክርስቶስ አካል መሆኗ። እያንዳንዳችን ምንም ያህል ኃጢአተኞች ልንሆን እንችላለን፤ ነገም፤ የምእመናን አንድነት ቅድስት ቤተክርስቲያን ግን ንጽሕት፣ ቅድስት ናት። ይህም ከእኛ የመጣ ቅድስና ሳይሆን አካሉ በሆነች በቤተክርስቲያን ራሷ ሆኖ በመካከላችን ካለው ከክርስቶስ የተገኘ ነው። ከኃጢአት የማንጠራ ጉስቋሎች ብንሆንም በመሰባሰባችን «የምትፈጠር» ቅድስት ቤተክርስቲያን ግን በእውነት ንጽሕት ናት፤ የሕመሟ መድኃኒት፣ የቅድሰናዋ ምንጭ በመካከል ነውና።

በምእመናን መሰባሰብ «የተገነባች» ቤተክርስቲያን «ቅዱስ ሕዝብ፣ የንጉሥ ካህናት፣ የተመረጠ ዘር..»[3]መባል ይገባታል፤ የመረጣት ከኃጢአት ባርነት አውጥቶ ያከበራት የቅድሰናዋ አክሊል በመካከሏ ነውና።

ለዚህ ነው በሐዋርያት ዘመን የነበሩ ምእመናን «ቅዱሳን» ይባባሉ የነበሩት፤ በመሰባሰብ ይኖሩ ነበረና።

---

1. Fr. Alexander Schememan, The Eucharist, pp21
2. « when I say that I am going to church, it means I am going into the assembly of the faithful in order, together with them, to constitute the church, in order to be what I became on the day of my baptism a member, in the fullest, absolute meaning of the term, of the body of Christ» ibid, pp.23
3. 1ኛ. ጴጥ.2 ፥9

ይህ የቅድስና መዓዛ፣ ይህ ሰማያዊ ደስታ ነበረ መራራውን መከራ በደስታ እንዲቀበሉት ያሰቸላቸው ይህ የቅድሰና ጉባኤ የቤተክርስቲያን ሰማያዊ ደሰታ ነበር፣ በአስቸጋሪው ዓለም ክርስትናን በቆራጥነት እንዲሰብኩ ያስቻላቸው፡፡ «የቤተክርስቲያን የማኀበሯ ፍፃሜ» ይህ ነውና፡፡

የምእመናን መሰባሰብ የክርስቶስን አካል እንደሚገልጥ፣ ቅዳሴውን የሚመራው ካህን ራስ የተባለ የክርስቶስን ክህነት ይገልጣል፡፡[1] የጌታችን ክህነት በውክልና ለሌላ የማይሰጥ፣ ከራሱ ከክርስቶስ ውጪ ለሌላ የማይገባ ዘላለማዊ ገንዘቡ ነው፡፡ በካህኑ የሚገለጠው የክህነት ኀይል ከክርስቶስ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ መገኘትና በካህኑ በኩል መገለጥ የመጣ ነው፡፡ ካህኑ የሚለብሰው የክህነት ልብስ፣ ክርስቶስ በውስጧ ያደረው የቤተክርስቲያን መገለጫ ነው፡፡ ለዚህ ነው፤ በቤተክርስቲያን ሥርዓት ምእመናን ሳይሰበሰቡ ልብስ ተክህኖ መልበስ የተከለከለው፡፡[2] በካህኑ ራስ ላይ ያለው አክሊል እንደ መልከጼዴቅ ሥርዓት ያለውን ዘላለማዊውን የክርስቶስ ክህነት ይገልጣል፤ መልኬ ጼዴቅ የሳሌም ንጉሥና የህያው እግዚአብሔር ካህን ነበረና፡፡[3] እንግዲህ የጌታችን ዘላለማዊ ክህነት በዘላለማዊና ሰማያዊ መቅደሱ በቅድስት ቤተክርስቲያን በዚህ መልኩ ይገለጣል ፤ ቅዱስ ጳውሎስ «እርሱ ግን የማይለወጥ ክህነት አለው፤ ስለኛ ሊያማልድ» ዘወትር በሕይወት ይኖራል..» እንዳለ፡፡[4]

በመጨረሻ፣ እግዚአብሔር በሚያሳየው ምድር በደስታ ይኖር ዘንድ አብርሃም ወገኖቹንና የአባቱን ቤት እንዲተው ከታዘዘ[5]፣ ወደ አግዘብሔር መገለጫ፣ ወደ ጸዮን ተራራ ስንወጣ የበኩራትን ማኀበር[5] ልንመሠረት ስንሰባሰብ እንዴት አለማዊ ጣጣችን አንተው? እስራኤል በሲና ተራራ በሚያሰፈራ ሁኔታ የተገለጠውን እግዚአብሔርን ለመስማት ሦስት ቀን ከተዘጋጁ[7] ልብሳቸውን ካጠቡ፣ በሚያስደንቅ የመሰዋዕትነት ፍቅሩ ስለኛ የተሰቀለውን አምላካችን ለማየት ብቻ ሳይሆን ለመብላት ለመጠጣት ስንሰባሰብ ምን ያህል መዘጋጀት፣ ልብሳችን ብቻ ሳይሆን ሰውታችን ምን ያህል በንስሐ ማጠብ ይገባን ይሆን? ህፃኑ ሳሙኤል በቤተመቅደስ ለሚጠራው ቃል በንቃት መልስ ከሰጠ[8]፣ በእውነተኛ ቤተመቅደሱ የተሰበሰብን እኛ በቅዳሴ ሰዓት በልዩ ልዩ መንገድ ለሚሰማው የእግዚአብሔር ድምጽ ምን ያህል በትጋትና በንቃት መልስ መስጠት ይኖርብን ይህን?

---

1. ኤፌ. 5፥23፣ 1ቆሮ. 11፥3
2. መጽሐፈ ቅዳሴ
3. ዕብ.7፥ 20 - 22፣ መዝ.109፥ 4፣ ዕብ.7 ፥ 1
4. ዕብ.7፥ 25
5. ዘፍ.12፥ 1
6. ዕብ.12፥ 22-24
7. ዘፀ.19፥ 14-15
8. 1ኛ.ሳሙ. 3፥ 1-14

.........ይቆየን.......